**ዶክተር አብይና የሚመሯት ኢትዮጵያ!**

ጓደኛህን ንገረኝና ማንነት ህን ልንገርህ  የሚል የቆየ የ አገራችን አባባል አለ።በሌላ በኩን ትምህርት ምንድነው የሚል ጥያቄ  ብንጠየቅ ሳይንሳዊ መልሱ ትምህርት የባህሪ ለውጥ ነው  በማለት ከመለስን ትክክል ነን። የባህሪ ለውጥ ሲባል ደግሞ ከነበረን አመለካከት ወይም ግንዛቤ ወደሌላ አመለካከት መለዎጥ ወይም መቀየር ማለት ይሆናል። ስለዚህ ደጋግመን የምናነባቸው፣ ደጋግመን የምንሰማቸውና ደጋግመን የምንለማመዳቸው ነገሮች ባህሪያችንን ይወስኑታል። አንዳንዴ ዶክተር ወይም ኢንጅነር ፣ ማስተር ወይም ዲግሪ ተመርቀዋል የምንላቸው ሰዎች  ያስቡታል ብለን የማንገምተውን ተራ ነገር ሲያዎሩ ስንሰማ እንሸማቀቃለን። ይህ ሰው የተማረ አይደለምን ብለንም እንጠይቃለን ። ትምህርት የባህሪ ለውጥ ነው የሚለውን የትምህርት ትርጉምም በ አንድ አይነት አቅጣጫ ብቻ ስለምንረዳው ግራ እንጋባለን። የምንማረው ነገር የምናነብበውን የምንሰማው ጉዳይ ባህርያችንን እንደሚዎስነው ግን እንዘነጋለን።ለምሳሌ ዐማራ መደራጀት አለበት ብለን የምንሞግት ሰዎች ምክን ያታችን ዐማራ የበላይ መሆን ይገባዋል የሚል ቅንጣት ያክል ሃሳብ እንደሌለን እኛ ብቻ ሳንሆን ብዙዎች ያዉቁታል። ታሪክን ሳይዛባ የሚገነዘቡ ሁሉ ይህንን የዐማራ መደራጀት ፈጽሞ ይረዱታል።ዐማራ መደራጀት አለበት ብሎ የሚሰብክ የትኛውም የሙብት ተሟጋች ወይም የታሪክ ሰው እኩልነትን ፍት ህንና ነጻነትን የሚደግፍ ራሱን ከመጥፋት ለመታደግ የሚሻ ብቻ ነው። በዚህ መደራጀት ለሌላው ስጋት የለም። አከሌ ስለበደለህ አንተም ተራህን አከሌን መበደል አለብህ የሚል ትርክት የለውም። ዐማራ እንዲደራጅ የሚመኝና የምጠይቅ ሁሉ ኢትዮጵያን የሚዎድ  በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራና ፍት ህን የተጠማ ነው። ስለዚህ በዐማራ መደራጀት ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ከ ጥቂት የዋሃን በስተቀር አብዛኞቹ አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም አይነት ሰዎች ናቸው።

ከብዙ ታሪክ አዋቂ ነጮች ጋር በ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ተወያይቼ አውቃለሁ። የዐማራ ብሄርተኝነት ጠንካራ ኢትዮጵያን እንደሚፈጥር አንዳቸውም ጥርጣሬ የላቸውም። ታዲያ ይህንን እያወቁ አፍራሽና ጠባብ ጎሰኞችን በዚያች አገር ፖለቲካ ተዋናይ እንዲሆኑ ለምን እንደሚረዱ ስጠይቃቸው አንዳቸውም አጥጋቢ መልስ አይሰጡኝም። ከዎራት በፊት በኔዘርላንድስ የላይደን ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ጥናት ዳይሬክተር የሆኑትና የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርብ ከሚከታተሉት ፕሮፌሰር ጋር በነበረኝ ውይይት  የ ዐማራ ብሄራዊ ንቅናቄ አደረጃጀትና አካሄድ  እጅግ እንዳስፈራቸው ነገር ግን ለጠንካራ ኢትዮጵያዊነት መሰረት እነደሚሆን ያስረዱበት መንገድ በጣም አስገርሞኝ ነበር። አስፈሪ ነገር ግን ለጠንካራ ኢትዮጵያዊነት መሰረት  በእርግጥም አስገራሚ አገላለጽ።የህወሃት ኢህ አዴግ መንግስት ስለዘረኝነቱ ከፋፋይነቱና ሴረኝነቱ በርካታ ማስረጃወችን መደርደር ለቀባሪው አረዱት አይነት አገላለጽ ቢመስልብኝም ይህ ተፈጥሮው ከሶስት ዋና ዋና ምክን ያቶች ይመነጫል።

1. ደጋፊዎች የነበሩት የውጪ መንግስታት የተረጋጋችና ጠንካራ ኢትዮጵያ እንዳትኖር የሚፈልጉ መሆናቸው
2. የህወሃት ዋና አላማ ትግራይን ነጻ ማውጣት የሚል መሆኑና
3. ለአላማው ግብ መምታት ዋና ስትራቴጅው ሌሎች ኢትዮጵያውያን እንዳይተማመኑ በጎሳና በሃሰት ታሪክ እንዲ ጠመቁ ማድረግ ስለነበረ ነው።

**ጥቂት ስለራሴ አመለካከትና ዶክተር አብይ ወደስልጣን ሲመጡ ስለነበረኝ የለውጥ ተስፋ**

አቶ ለማ መገርሳ **ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው** በማለት ባህርዳር ላይ ሲናገሩ ዶክተር አብይ ደግሞ **ስንኖር ኢትዮጵያውያን ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ እንሆናለን** በማለት ለበርካታ አመታት ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ሳይሰማ የኖረውን ንጹህ ኢትዮጵያዊ ሲያስፈነጥዙና ከጫፍ ጫፍ ህዝቡ ድጋፉን ሲገልጽላቸው ለማመን ተስኖኝ ነበር። በአንድ በኩል ስለኢትዮጵያዊነት  ከከፍተኛ ባለስልጣናት በተለይም  ደግሞ ቢያንስ ለ30 አመታት ኢትዮጵያ እንዳይል በሃሰት ታሪክ ሲጋት ከኖረው ሆን ተብሎ ከጎሳው ውጭ እንዳይመለከት ከፍተኛ የካድሬ ስብከት ማረፊያ ከነበረው ከኦሮሞ በመስማቴ ደስ

ቢለኝም የኢህ አዴግን አፈጣጠርና የሴራ ፖለቲካ በቅርብ ስገነዘበው የኖርኩት ስለነበር አንዳች የተሸረበ ሴራ ይኖር ይሆን በሚል ጥርጣሬ ውስጥ ነበርኩ። ለበርካታ ወራትም ሁሉም በድጋፍ ዶክተር አብይን ሲያንበሸብሽ በተለይ ፍራንክፈርት ሄጄ የዶክተር ዐብይን ንግግር እስክሰማ ድረስ ለውጡን መደገፍ ለእኔ ከባድ ነበር።

በዚህ በኢትዮፖትርዮትስ **እኔና ፍራንክፈርት** በሚል ርእስ እንደጽፍኩትም ለዶክተር ዐብይ ምእራባውያን ከፍተኛ ድጋፍ እንዳላቸው ተገነዘብኩ ። ቢያንስ ዶክተር አብይን አለማመን ተገቢ አይደለም የሚል ድምዳሜ ደርሼም ነበር። ይህ አመለካከቴ ከሁለት ነገሮች ይመነጫል። ጠንካራ የመጽሃፍ ቅዱስ አማኝ በመሆናቸውና በተደጋጋሚ ለፍትህ ስላላቸው አዎንታዊ አቋም።

**አሁንስ?**

ዐማራውን ከኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ለማስወገድ በተሰራው ከፍተኛና መዋቅራዊ እንቅስቃሴ መጠን በኦሮሞው ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የተበዳይነትና የጎሰኝነት ስሜት እንዲያድግ ተሰርቷል። ኦሮሞ ጎሳየ እንጂ አገሬ እንዳይል ፣ የእኔ እንጂ የእኛ እንዳይል ከተስፋየ ገብረአብ ልቦለደች ጀምሮ እስከ የተለያዩ የካድሬ ስልጠናዎች ተሰብኳል። ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ በተለያዩ ቤተ እምንቶች አማርኛ ቋንቋ የረገጡህና የገዙህ የእነ ምኒልክ ስለሆነ እንዳትጠቀምበት በመባሉ ይህንን ትርክት ሳያጣራ እንዲውጠው ተደርጓል። እያንዳንዱ የኦሮሞ ካድሪ እና ማንበብና መጻፍ የሚችል ሁሉ " **ኦሮሚያ የተደበቀው ይግፍ ታሪክ ክፍል አንድና ሁለት** " በሚል ርእስ **በወልደዮሃንስ ወርቅነህና ገመቹ መልካ** የተጻፈ በሬ ወለደ የሃሰት ታሪክ እንዲጋት ተደርጓል።በቅርቡ አቶ ሌጮ ባቲ እንደተናገሩት በነበረው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ **ኢትዮጵያን ዝቅ** በማድረግ **ኦሮሞን ከፍ የማድረግ** ዲስኮርስ ተጠቅመናል በዚህም ኦሮሞን የማደራጀቱ ጉዳይ ተሳክቶልናል ብለዋል።አያይዘውም አቶ ሌንጮ ሌላውን ኢትዮጵያዊ በመያዝ ግን አልተሳካልንም፣ ይህ የተሳካላቸው ዶክተር አብይና አቶ ለማ ናቸው። አሁን ኦሮሞ ያልተመለሰ ስትራክቸራዊ ችግር የለበትም በማለት እውነታውን ቁጭ አድርገውታል።እዚህ ላይ መረዳት ያለብን እውነት ላለፉት ቢያንስ አርባ አመታት በኦሮሞ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ዘንድ ኢትዮጵያን ዝቅ የማድረግ ስብከት መሰበኩን ነው። ይህ ትምህርት የአብዛኞቹን ኦሮሞዎች ባህሪ ቢለውጥ የሚገርም ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ትምህርት ባህርይን መለዎጡ ሳይንሳዊ ስለሆነ። ሌላው ቀርቶ ታላቋ ኢትዮጵያ ከኦሮሞ አብራክ በዎጡት በእነ ዶክተር ዐብይ እየተመራች እያለ ኢትዮጵያ የኦሮሞ ነች ማለት ሲገባ አዲስ አበባ የኦሮሞ ነች የሚል ጠባብና የዝቅተኝነት ወይም ያለመረጋጋት ሜዳን ማስፋት ከሌላ ከየትም የመጣ ሳይሆን ላለፉት በርካታ አመታት ከተሰበከው የተቀምቻለሁ የሃሰት ትምህርት የመነጬ ነው።በኦሮሞ ህዝብና በተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል በተለይም በዐማራና በኦሮሞ መካከል የተዘራው ክፉ ዘር ተነቅሎ የማያልቅ በርካት ስንክሳሮችን የያዘ ነው። የአዲስ አበባ የባለበትነት ጉዳይ፣ ኢትዮጵያ ለዘመናት የምትታወቅበትን ባንዲራ ኦሮሞዎች የራሴ እንዳይሉት ሆን ተብሎ የተሰራው ክፋት፣ በአብፍሪካ ብቸኛ የፍደል ባለቤት የሆነች ኢትዮጵያችን በብሄራዊ ደረጃ ክልሎች ሁሉ ፊደሉን የማይጠቀሙበት ምክን ያት፣አለም የተደነቀላቸው የነጻነት ተምሳሌ የሆኑት ታላቅ መሪ ምኒልክ ሆን ተብሎ በኦሮሞ ወንድሞቻችን ገዳይህ ነበሩ ተብሎ የተነገረው ትርክት፣ በአርሲ የቆመው የአኖሌ የጥላቻ ሃውልት፣ ባለፉት ወራት ተግባራዊ እየሆነ ያለው በተለይም ጎሳንና ነገድን ያማከለው አዲስ አበባን ጨምሮ ከአዲስ አበባ ዙሪያ የሚደረግ የተደራጀ የማፈናቀል ተግባር፣የሚቆም አይመስልም።የለውጥ መሃንዲስ የሚባሉት አቶ ለማና ዶክተር ዐብይም ከእባብ እንቁላል እርግብ አይገኝም አይነት ሆነዋል። በተለይ ዶክተር አብይ አንደበተ ርቱዕነታቸው በቀረው ኢትዮጵያዊ ያስገኘላቸው ታዋቂነትና ድጋፍ በአጭር እንዲሸረሸርባቸው እያደርጉ ያሉ ምክን ያቶችን መጠቆም እወዳለሁ። ከሁሉ ይልቅ ሰሞኑን በለገጣፎ ማፈናቀል ዙሪያ የሰጡት አስተያየት ሰውየው ወዴት እየሄዱ ነው እንድንል አድርጎናል። በለገጣፎ አሉ ዶክተር አብይ በለገጣፎ የተደረገውንና የታቀደውን የተሰራውንም አላውቅም ነበር በማለት እጁ እስኪላጥ አጨብጭቦ የደገፋቸውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ አሹፈውበታል። ከሁለት አመት በፊት ፊንፊኔ የኦሮሞ ናት በማለት ሸንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስተራችን አገር የመምራቱን ሃላፊነት በወሰዱ በአስር ወራቸው በፊንፊኔ ዙሪያ የታቀደውንም

የሚሰራውንም አላውቅም በማለት በአደባባይ መናገራቸው በርካታ ሰዎች በጥርጣሬ እንዲመለከቷቸው በራሳ ቸው ጊዜ ራሳቸውን አጋልጠዋል።

ታከለ ኡማ ወደስልጣን ሲመጡ ህግን በአንዲት ጀምበር በፓርላማ ያስጸደቁት ዶክተር አብይ ሚሊየኖች ኢትዮጵያ በማለታቸው የቸሯቸውን ድጋፍ ለማካካስ እንኳ ሚሊየኖች የሚይጠሉትን ህገመንግስት ለማሻሻል ፓርላማቸውን ለማሳመን ያደረጉት እንቅስቃሴ የለም። ይልቁንም በሊቀመንበርነት የሚመሩት ኦዴፓ በፌደራሊዝሙ ከማንም ጋር አልደራደርም የሚል መግለጫ እንዲያወጣ አድረገው አሳፍረውናል። በደገፋቸው ህዝብ ማሸፍን የቀጠሉት ዶክተር አብይ ፓርቲያቸው በፌድራሊዝሙ አልደራደርም የሚል መግለጫ እንዲያወጣ ካደረጉ በኋላ በማግስቱ ከጥቂት ወራት በኋላ የዐማራ፣ የኦሮሞ፣ የአፋር ወዘተ የሚባል ፓርቲ አይኖርም ፣ አንድ አገራዊ ፓርቲ እንመሰርታለን በማለት እንድንደናገር አድርገውናል። ዘመድኩን በቀለ የተባሉ ጸሃፊ የካቲት 13 ቀን 2011 ዓም ‘’**ህዝብ ያደነዘዘ ፣ ታማኝ በየነን እግር ያሳመ ፣ ኢሳትን ኢቢሲ ያደረገ ዶክተር ብርሃኑን አዲስ አበባ ወስዶ ያሰረ አብይ አህመድ የኦሮሞ ጀግና ነው**’’ በሚል ርዕስ በዎልቃይት ዶት ኮም እደጠቆሙት ‘’ እርካብና መንበር ‘’ በተባለ መጽሃፋቸው የገለጹትን የአስተዳደር ጥበብ ዶክተር አብይ እየተገበሩብን ያሉ ይመስላል። ስለዚህም አሁን ዶክተር አብይን ከላይ በዘረዘርኳቸውና በተለያዩ ምክንያቶች ልጠራጠራቸው ችያለሁ። አሁንም ኢትዮጵያችን የሁላችን እስክት ሆን ድረስ የትኛውም ዜጋ ከገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ በነጻነት የመኖሩና የመንቀሳቀሱ መብት እስኪረጋገጥ ድረስ የሚፈጸሙ ሻጥሮችንና ፍት ህ አልባ ድርጊቶችን ከመጠቆም ከፋፋይና ሁሉንም አካታች ያልሆነው ህገ መንግስት እስኪቀየር ድረስ መወትዎቴን አልተውም።

**ማጠቃለያ**

ዶክተር አብይ የመንደራቸውን ሰዎች ሰብስበው ‘’ **ነጮች እናንተ ከጎሳችሁ ወጪ አታስቡም፤ አገር መምራት አትችሉም በማለት ያሸማቅቁናል። አሁን አገር መምራት እንደምንችል ልናሳያቸው ይገባል**’’ በማለት ሲናገሩ ሰምተናቸዋል። ልክ ነው አገር መምራት ከጎሰኝነት የዘለለ አስተሳሰብን ይጠይቃል። ልክ ነው አገር መምራት ሁሉንም በአገሪቱ ያለን ዜጋ እኩል ማየትን ይጠይቃል። አወ አገር መምራት አገራዊ ማንነትን ያጎላል እንጂ በቋንቋና በዘር የተከፋፈለን ፌደራሊዘም እንደ መጽሃፍ ቅዱስ ወይም እንደ ቁራን አይነኬ አድርጎ ለብዙዎች መፈናቀልና መገደል ምክንያት እንዲሆን አይፈቅድም። የሀገር መሪ መሆን በሃሰት የተገነቡ ሃውልቶችን ማፍረስና እውነተኛ ትርክቶች ታሪክን እንዲቆጣጠሩ ይፈቅዳል እንጂ የሀሰት ትርክቶች እንዲቀጥሉ አይፈቅድም። አገር መምራት በዜጎች መካከል ልዩነት መፍጠርን ይኮንናል። የተደበቀ ሳይገለጥ የሚቀር ነገር የለም ። አንድነት፣ አገሬ፣ ባንዲራየ ያሉ ከ3000 በላይ የአዲስ አበባ ወጣቶች ኦነግንና ባንዲራውን አወገዛችሁ ተብለው ዛሬም በእስር ቤት እንደሚገኙ በርካታ የዐማራ ፖለቲከኞችና ወጣቶች ዛሬም በእስር ቤት እንዳሉ እየተነገረ ነው። ለነገሩ ከ2000 በላይ የሆኑ ነዋሪ ያልነበሩ በአዲስ አበባ የነዋሪነት መታወቂያ እንዲሰጣቸው የፈቀደ ይህንንም አስተዳደር ሃይ ያላለ የአገር መሪ ሌሎች በርካታ አድሎአዊ ስራዎች እንዲሰሩ አይፈቅድም ለማለት መራላዊ ብቃት አይኖርም።

ሁላችን እንደሰማነው የለጋጣፎ ከንቲባ ስለ ቤት ማፍረሱና ዜጎችን ማፈናቀል በትእቢት ሲናገሩ በአግድሞሽ ብሄርን ለይቶ የተደረገ ስለመሆኑ ነውግረውናል።አዎ ቤት የፈረሰባቸው ተፈናቀሉ ተብሎ ከሚጮህላቸው ሁለት ብሄሮች የመጡ ስለሆነ ነው ብለዋል። ቅኔው አማራና ትግሬ ማለታቸው ነው። ይህንን ስሰማ በእርግጥም ኢትዮጵያ በተቀበረው የዘር መርዝ እየተባላች ያለች አሣዛኝ አገር እንደሆነችና ረዥም ትግል ከፊታችን እንደሚጠብቀን ነው፣ ላለፉት ሃያ ሰባት አመት በስሙ ሲነገድበት የኖረው የትግራይ ህዝብም ሆነ በሃሰት ትርክት ጡት ቆራጭ ርስት ዘራፊ እየተባለ የሀሰት ፕሮፓጋንንዳና ጥላቻ ሲዘራበት የኖረው የዐማራ ህዝብ በዘመነኞቹ ደግሞ ቤቱ እየፈረሰ ንብረቱ እየተዘረፈ የጎዳና ተዳዳሪ ሊሆን አይገባውም። ዘረኝነትና አድሎአዊነትን መዋጋት የሀገር መሪዎቻችን ዋና ትኩራታቸው ሊሆን ይገባል።

አበቃሁ!

አስተያየትና ምክር ካላችሁ

addiste@gmail.com ጻፉልኝ

አዲስ ተስፋ

የካቲት 2011